Amharic | አማርኛ

homes victoria

VICTORIA State Government | Families, Fairness and Housing

## የሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታ

# የማህበረሰብ ጋዜጣ

ታህሳስ 2023





በካርልተን ውስጥ ጡረታ የወጡት ሁለቱ "የቀይ ጡቦች" ማማዎች ከአየር ላይ የተወሰደ ምስል

በዚህ እትም፣ የአዳዲስ ቤቶች እቅድ ተዘጋጅቷል፣ በካርልተን ውስጥ የመጀመሪያው ሰማይ ጠቀስ ፎቅ መልሶ ግንባታ ይካሄዳል፣ ከዚያም ፕረሃን፣ ሳውዝ ያራ፣ ፖርት ሜልበርን እና ሃምፕተን ኢስት ላይ የቢግ ሃውሲንግ ቢዩልድ (Big Housing Build) ስራ የቀጥላል። ሁሉም የበለጡ እና የተሻሉ ቤቶችን ለብዙ ቪክቶሪያውያን ያቀርባሉ።

እንዲሁም የተከራይ ድምጽ እንዴት ለሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንዳለ እንሽፍናለን።

## ብዙ እና የተሻሉ የህዝብ መኖሪያ ቤቶች በካርልተን

ጠቅላይ ሚኒስትር አንቶኒ አልበኒዚ እና የቀድሞ ቀዳሚ ሚኒስትር ዳንኤል አንድሪውስ በካርልተን ውስጥ ጡረታ የወጡትን የህዝብ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ቤቶችን እንደገና ለመገንባት ማቀዳቸውን አስታውቀዋል። እነዚህ በፕሮግራሙ ውስጥ እንደገና የሚገነቡት የመጀመሪያዎቹ ማማዎች ናቸው እና በ 2028 ይጠናቀቃሉ።

በኒኮልሰን እና በኤልጊን ጎዳናዎች ጥግ ላይ የሚገኙት የካርልተን ቀይ ጡቦች ሕንፃዎች ከ1960ዎቹ ጀምሮ የተሰሩ ሲሆን ከ2021 ጀምሮ ተከራዮች ከእድሜ ጋር በተዛመደ የሕንፃዎቹን ስርዓት መፈራረስ ተከትሎ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ተደርገዋል።

እነዚህ 196 ከአሁን በኋላ ለመጠቀም የማይመጥኑ መኖሪያ ቤቶች በዘመናዊ፣ ኃይል ቆጣቢ እና ተደራሽ ቤቶች ይተካሉ፣ ይህም በዚህ ጣቢያ ቢያንስ 16% ተጨማሪ የሕዝብ መኖሪያ ቤቶችን እንዲቀርቡ ያደርጋል።

**በ2024 መጀመሪያ**
የማህበረሰብ ተሳትፎ (የመጀመሪያ እይታ)

**2024**
የግንባታ ቦታ ዝግጅት ስራዎች

**2024**
በንድፍ ላይ የማህበረሰብ ተሳትፎ

**2025**
ግንባት የሚጀምረው

**2028**
የደረሱ አዳዲስ ቤቶች

ሆምስ ቪክቶሪያ ይህ መኖሪያ ቤት እየተገነባ ያለበትን መሬት የባህላዊ ጠባቂዎች እውቅና ይሰጣል። ላለፉት እና አሁን ላሉት ሽማግሌዎቻቸው ክብር እንሰጣለን።

# የተከራይ ድምጽ የነዚህን ሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታ ይመራል።



## ግንኙነቶችን ለማሻሻል የተከራዮች ግምገማ

በፍሌምንግተን እና በሰሜን ሜልበርን የሚገኘው ፔቪንግ ዘ ወይ (Paving the Way) ፕሮግራም በግንኙነቶች እና በተከራይ ድምጽ ላይ ግምገማ እና ማሻሻልን እያስተናገደ ነው።

አሁን ትኩረቱ ነዋሪዎችን ከቦታ ወደ ቦታ የማዛወር ሂደቱን መደገፍ፣ ምን አይነት መረጃ መቅረብ እንዳለበት መፈተሽ፣ እንዴት እንደሚተረጎም እና እንዴት ለህብረተሰቡ መረጃን በተሻለ መንገድ መስጠት እንደሚቻል መመልከት ነው።

## ለእርስዎ ግድ የሚልዎት (በጣም አስፈላጊ ነገር) ምንድን ነው? የጋራ-ንድፍ የማህበረሰብ መርሆዎች

የተከራይ ድምጽ ለሰማይ ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ንድፍ እና አቅርቦት ማዕከላዊ ነው። ለዛ ነው መርሆዎችን ለማቋቋም ከተከራዮች ጋር እየተገናኘን ያለነው። እነዚህ መርሆዎች ቀደም ብሎ እቅድ ማውጣትን፣ የተከራይ ወደ አዲስ ቦታ የመንቀሳቀስ መብትን፣ የህንጻ ግንባታን እንዲሁም የተከራዮች ወደ አዲስ ቤቶች መመለስን ይመራሉ።

በቅርብ ጊዜ በሁሉም ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ባላቸው ቦታዎች ከ100ዎች ተከራዮች ጋር አውደ-ጥናቶችን እና የውይይት መድረኮችን አድርገናል። ለእርስዎ ጠቃሚ የሆኑ እሴቶችን፣ እንዴት ተባብረን እንደምንሰራ እና ቅድሚያ ልንሰጣቸው የሚገቡ ውጤቶችን ጨምሮ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትልቅ ግብአት ሰምተናል።

በ2024 መጀመሪያ ላይ ከሁሉም ተከራዮች እና በዙሪያው ካሉ ማህበረሰቦች ጋር በረቂቅ መርሆች ላይ እንወያያለን።

በአካባቢዎ ስለሚመጡ የመሠረታዊ ተሳትፎ ክስተቶች ይወቁ።

**homes.vic.gov.au/high-rise-redevelopment-community-engagement**ን ይጎብኙ

**ህዳር 2023**
ከማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት

**ህዳር/ታህሳስ 2023**
አውደ-ጥናቶች ከተከራይ ድምጽ ቡድኖች ጋር

**በ2024 መጀመሪያ**
በረቂቁ የማህበረሰብ መርሆች ላይ ተሳትፎ

**መጋቢት 2024**
የመጨረሻ የማህበረሰብ መርሆዎች ታትመዋል



*በሰሜን ሜልበርን እና በፍሌምንግተን ማህበረሰብ የጥያቄ እና መልስ መድረኮች ከተከራዮች ጋር መነጋገር*



*በሲመንዝ ጎዳና፣ ሳውዝ ያራ ላይ ያሉ የአዲሶቹ ቤቶች የአርቲስት እይታ*

# ለሜልበርን ደቡብ-ምስራቅ የበለጠ ጥራት ያላቸው ቤቶች

**የሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ግንባታ ሂደት ላይ እያለ፣ አዳዲስ እና የተሻሉ ቤቶችን በቢግ ሃውሲንግ ቢዩልድ ፕሮግራም በኩል በማቅረብ ላይ እንገኛለን። በሳውዝ ያራ፣ ፕራሃን፣ ፖርት ሜልቦርን እና ሃምፕተን ኢስት የተሰሩ ከ1300 በላይ አዳዲስ ቤቶች በእነዚህ አከባቢዎች ላይ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶችን ቢያንስ በ31 በመቶ እያሳደጉ ነው። ይህ 56 ልዩ የአካል ጉዳተኞች መኖሪያ ቤቶችን ያጠቃልላል።**

ይህ ከህንፃ ማህበረሰቦች ጋር ያለው ሽርክና ጥራት ያለው የተከራይና አከራይ አስተዳደር፣ የማህበረሰብ ህንፃ እና ልዩ ድጋፎችን ለማቅረብ የሚሰሩትን እና ልዩ ድጋፍን  የሚሰጡትን ሃውሲንግ ቪክቶሪያ ሊሚትድ እና ከሴቶች ንብረት ተነሳሽነት (Women's Property Initiatives) እና ከአቦርጂናል ኮሚኒቲ ሃውሲንግ ቪክቶሪያን ያጠቃልላል።

## የነዚህ መድረኮች ቁልፍ ባህሪያት የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

**የማህበረሰብ ቦታዎች**

በግምት 2,000 ካሬ ሜትር የሚሆን ክፍት የአትክልት ቦታዎች።

**1፣ 2፣ 3** እና **4** መኝታ ቤቶች ያላቸው ቤቶች

ተከራዮች ለፕራሃን እና ለሳውዝ ያራ ቦታዎች ወደፊት እቅድ ትልቅ ግብአት ሰጥተዋል። በ2024 መጀመሪያ ላይ በፖርት ሜልቦርን እና ሃምፕተን ኢስት ላይ ተጨማሪ ተሳትፎ ለማድረግ እንዲሁም በ2024 መገባደጃ ላይ ግንባታ እንደሚጀምር እንጠብቃለን።

## በአቅራቢያዎ ባሉ ዝግጅቶች ላይ መገናኘት

ለእርስዎ በሚመችዎ ቦታ እርስዎን ለማዳመጥ እና ከርስዎ ጋር ለመነጋገር መገኘታችን ማረጋገጥ እንፈልጋለን። በሪችመንድ በቅርቡ በተካሄደው የወጋገን ገበያ ላይ መገኘት አጠቃላይ መረጃን ለመለዋወጥ እና ስለ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥሩ አጋጣሚ ነበር። በኤልዛቤት ጎዳና ስለሚሰሩትም 144 አዳዲስ ቤቶችም ከነዋሪዎች ጋር ተነጋገርን።

እንደተለመደው የሰሜን ሪችመንድ ማህበረሰብ የሰሜን ሪችመንድ ማህበረሰብ የድጋፍ ገንዘብ (North Richmond Community Grants) ለመጀመር ደስታን አምጥቷል። ሁሉም ሰው በጨዋታዎቹ፣ በምግቡ እና በጭፈራ ይዝናና ነበር!




*በሪችመንድ የምሽት ገበያ ከሰማይ ጠቀስ ፎቆች ተከራዮቻችን ጋር መሳተፍ*




## ከቦታ ወደ ቦታ የመዛወር ወቅታዊ መረጃ

በተገለጸው የፍሌምንግተን እና የሰሜን ሜልበርን ከፍተኛ ፎቆች ላይ የሚያዛውረው ቡድን ከ485 አባወራዎች ከ440 በላይ የሚሆኑት ጋር ተገናኝቶ እነዚህን ተከራዮች በመዛወር እቅዶች እና ማመልከቻዎች እየደገፈ ነው።

በቅርብ ጊዜ በእነዚህ ቦታዎች ላይ በሚሰሩት አዳዲስ ቤቶች ላይ ብዙ ፍላጎት ነበረ።  ከቦታ ወደ ቦታ ከሚያዛውረው ቡድን ጋር ለተገናኙ እና እንደ ፍላጎታቸው እና ምርጫቸው በአካባቢው ወይም በሌሎች አካባቢዎች ያለው አቅርቦት ለመቀበል ፈቃደኝነታቸው ለገለጹ ተከራዮች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ሊጀመር ነው።

በአሁኑ ጊዜ መዛወር ለማያስፈልጋቸው በሌሎች አካባቢዎች ላሉ ቤተሰቦች አሁንም ምክር እና ድጋፍ ለመስጠት እየተጣጣርን ነው።

**ከቦታ ወደ ቦታ ስለ መዛወር ለማሰብ ጊዜው ሲደርስ፣ ልምድ ያለው ቡድናችን የሚከተሉትን ያደርጋል፡-**

- ብዙ ማስታወቂያ እና መረጃ ያቀርባል (በቋንቋዎም ጨምሮ)
- የግለሰብ ፍላጎቶችን እና ሁኔታዎችን ለመረዳት እርስዎን ያዳምጥዎታል
- አዲስ መኖሪያ ቤት ከተከራዮች ፍላጎቶች እና ምርጫዎች ጋር የሚጣጣሙ አማራጮች ላላቸው ተከራዮች ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል
- መፍትሄዎች የተከራይ ብዝሃነትን እና ባህልን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ያረጋግጣል
- ምርጫቸው ይህ ከሆነ አብረው እንዲቆዩ ብዙ ቤተሰቦችን ለመደገፍ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

## ቀጣይነት ያለው ጥገና እና እድሳት

ለማንኛውም አስቸኳይ ጥገና፣ እባክዎን የቤቶች ጥሪ ማእከልን በ **13 11 72** ያግኙ ወይም የሚከተለውን ይጎብኙ፡-

housing.vic.gov.au/repairs



## ተጨማሪ ይወቁ

ለበለጠ መረጃ፣ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እና በአጠገብዎ የሚደረጉ ፕሮግራሞች ለመመዝገብ ወይም በቋንቋዎ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ፡-

homes.vic.gov.au/high-rise-update-Dec-23

ስካን ያድርጉኝ

**enquiries@homes.vic.gov.au**

**1800 716 866**

የእኛን **@homesvic** የማህበራዊ መገናኛ ገጾች ይከተሉ

homes victoria

VICTORIA State Government

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place, Melbourne © የቪክቶሪያ ግዛት፣ ሆምስ ቪክቶሪያ (የቤቶች ዳይሬክተር)፣ ኦክቶበር 2023። የታተመው በፊንስበሪ ግሪን፣ ሜልበርን ቪክቶሪያ (HV023823)